## *በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ*
## *Coordinating Committee of Exiled Members of Ethiopian Teachers' Association*

*የተሰጠ መግለጫ*

*ጥር 28, 2005ዓ.ም*

*አገርን የመግደል፣ ትውልድን የማጥፋት ቀጣይ ሴራ።*

የወያኔ/ኢሕአዴግ ሥርዓት በአሁኑ ጊዜ በሁሉም የሥራ መስኮች ትኩረት ሰጥቶ እየተንቀሳቀሰበት ያለው በምርጫ 2002 ዓ.ም የተጠቀመበትን የተደራጀ የልማት ሠራዊት መገንባት በሚለው አንድ ለአምስት ፖለቲካዊ አደረጃጀቱ ተማሪዉን አንድ ለአምስት እንዲደራጁ በማድረግ ( በእያንዳንዱ የመንግሥት መስሪያ ቤት በገጠርና በከተማ ተግባራዊ እያደረገ ያለው የስርዓቱ የአደረጃጀት ዘዴ ነው) በኢሕአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ እንዲጠመቅ እርስ በርሱ እንዳይተማመን በጥርጣሬ ዐይን እንዲተያይ፣ በሃገር ጉዳይ ላይ በጋራ እንዳይመክር፣ በስርዓቱ ላይ ታቃውሞ እንዳያነሳ፣ የስርዓቱ አራማጅ ፣ ደጋፊና አገልጋይ ሆኖ እንዲቀጥል የዘረጋው የአፈና መዋቅር ትምህርት ቤቶችን አካዳማዊ እውቀት የሚገበይባቸው አምባዎች ሳይሆኑ የኢሕአዴግ የፖለቲካ አቀንቃኝ ተቋም እንዲሆኑ አድርጓቸዋል።

የወያኔ ሕገ መንግስት አንቀጽ 90 ንዑስ አንቀጽ 2 ትምህርት በማናቸውም ረገድ ከሃይማኖት ፣ ከፖለቲካ አመለካከቶችና ባሕላዊ ተፅዕኖዎች ነፃ በሆነ መንገድ መካሄድ አለበት ይላል። ሆኖም ግን ወያኔ ራሱ ያወጣውንና ቆሜለታለሁ የሚለውን ሕገ መንግስታዊ ድንጋጌ በመጣስ የየትምህርት ቤቶቹ ር/መምህራን በየትምህርት ቤቶቹ የሚገኙ የኢሕአዴግ አባል የሆኑ መምህራንና ሠራተኞች ህዋስ ሰብሳቢ በመሆን በዋነኛነት የፖለቲካ ሥራ እንዲሠሩ ከመመደባቸውም በላይ ሲገመገሙም ዋነኛ መገምገሚያው የፖለቲካውን ሥራ ሰርተሃል ፤ አልሰራህም የሚል ነው። ም/ር/መምህራን ደግሞ በግልጽ በትምህርት ውጤታቸው በየክፍሉ ከ 1ኛ እስከ 10ኛ ብሎም እስከ 20ኛ ደረጃ የወጡ ተማሪዎችን በግዳጅ በወጣት ሊግ በማደራጀት የኢሕአዴግ አባልነት ወርሃዊ ክፍያ በማስከፈል፤ ሰላይ ተማሪዎችን በየክፍሉ ውስጥ በመመደብ የስለላ ሥራ እንዲሰሩ በማሰማራት ተግባር ተጠምደዋል።

የስለላ ሥራው የኢሕአዴግ አባል ባልሆኑ መምህራንና ሰራተኞች እንድሁም ተማሪዎች ላይ የሚካሄድ ቢሆንም በዋነኝነት ግን ተቃዋሚ ናቸው ተብለው በሚጠረጠሩ መምህራን ላይ የጠነከረ ከመሆኑም ባሻገር በየእለቱ በክፍል ውስጥ የሚናገሯቸው የትምህርት ይዘት ያላቸው ቃላት እንደ ጸጉር እየተሰነጠቁ በየትምህርት ቤቶቹ ለተቋቋሙት የወያኔ/ኢህአዴግ ህዋስ የሃይል መድረክ እስከ ከፍተኛው የኢህአዴግ የፖለቲካ አመራር ሪፖርት እየተደረገ በእያንዳንዱ መምህር ስም ባዘጋጁት የግል ማህደር መዝገበው በመያዝ የትምህርት፣ የሥራ፣ የሥልጠና ፣ የእድገት ፣ .... ወዘተ እድል ሲመጣ የእድሉ ተጠቃሚ እንዳይሆን ነጥሎ ለመምታት ይጠቀሙበታል። ለምሳሌ በሰኔ ወር 2004 ዓ.ም ለ2ኛ ድግሪ የትምህርት እድል (ድህረ-ምረቃ) 30 ፐርሰንት ( 30%) የሚይዘው ሙያዊ ስነ ምግባርን በሚመለከተው የመወዳደሪያ መስፈርት ስር ፤ የስራ ተነሳሽነት 6% ፣ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ 6% ፣ ለሙያዊ ስነ ምግባር ተገዥነት 6% ፣ ለሌሎች አርዓያ የሆነ 6% ፣ ለለውጥ ዝግጁ የሆነ 6% የሚል ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸውን ሃረጎች በመጠቀም ያለምንም የመግቢያ ፈተና አባሎቻቸውንና ለዘብተኛ የሆኑ መምህራንን የትምህርት እድል ተጠቃሚዎች አድርገዋል።

የሥራ እድልን በተመለከተም ሁለተኛ ድግሪን የያዙ መምህራን በዩኒቨርስቲዎችና በኮሌጆች ለሚወዳደሩ ለስሙ ነፃ ውድድር ለማስመሰል የትምህርት መረጃዎችን እኩል እንዲያቀርቡ፤ ፈተናም እንዲፈተኑ ይደረግና በውስጥ ድርጅታዊ ሥራ በመስራት በፈተና የወደቀ በማስመሰል የሚፈልጓቸው የወያኔ/ኢህአዴግ አባልና ታማኝ የሆኑትን በማሳለፍ አባል ያልሆኑትን የእድሉ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ስውር ተንኮል በመፈጸም ላይ ይገኛሉ። በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ መምህሩ ለመኖር ከባድና አስቸጋሪ በሆነበት ሁኔታ ውስጥ እየሰራ በሃገሪቱ በተከሰተው የኑሮ ውድነትና የዋጋ ንረት አንፃር ኑሮውን በአግባቡ መምራት ስላቃተው የደመወዝ ጭማሪ እንዲደረግለት ላቀረበው ሕጋዊ ጥያቄ መምህሩ የደመወዝ ይጨመርልኝ ጥያቄ አላነሳም ያልተጠየቀውን አንመልስም ፤ የተጠየቅነው የደመወዝ ስኬል ማስተካከያ ነው፤ ይህን የደመወዝ ማስተካከያ 99.9% የሚሆኑ መምህራን ደግፈውታል እያሉ ማምታታት ቀጠሉ። ከ3 መቶና ከ4 መቶ ሺ ከሚሆኑት መምህራን የተቃወሙት 5 መቶ ያህል ናቸው ። አስር የማይሞሉ ከሥራ የታገዱት መምህራን የማስተማር ብቃት የሌላቸው የነውጠኞችና የሽብረተኞች ተላላኪዎች ስለሆኑ መባረራቸው ሳይሆን እርምጃው መዘግየቱ ነው ጥፋቱ በማለት ሟቹ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በመምህሩና በማስተማር ሙያ ላይ አፌዘውበታል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ አንዳንዶች የመምህርነት ሥራ ያልተሰካላቸው በሚልም በተለመደው ጋጠወጥ አባባላቸው ዘልፈዋል።ከተባረሩት መምህራን መካከል አንዱ በሚያስተምርበት ትምህርት ቤት ኮካብ ሠራተኛ መሆኑን የሚያመለክት ራሱን የቻለ መግለጫ በቅርቡ እንደምናወጣ በዚህ አጋጣሚ ለማስታወስ እንወዳለን።

የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር የካቲት 22 ቀን 2001 ዓ.ም ለ2002 ዓ.ም ምርጫ መጠቀሚያ እንዲሆኑላቸው በማሰብ ከመላው ሃገሪቱ ተወጣጥተው የተጠሩ ወደ 3 ሺ የሚሆኑ መምህራንን በጽ/ቤታቸው የስብሰባ አዳራሽ ሲያነጋግሩ “ አሁን የገበያው ሁኔታ ስላልተረጋጋ ደመወዝ ቢጨመርላችሁ ገንዘቡ ኪሳችሁ አያድርም፤ አይጠቅማችሁም። ገበያውን አረጋግተን ይጨመርላችኋል በጭማሪው የምትጠቀሙት ያኔ ነው “ በማለት የገቡትን ቃላቸውን ክደው ኢየሱስ ክርስቶስ ጴጥሮስን ዶሮ ሳይጮሕ ሶስት ጊዜ ትክደኛለህ እንዳለው የርሳቸውም ተግባር እንዲሁ ሆነ፡፡ በመምህራንና በትምህርቱ ላይ የጥፋት እርምጃው በስውርም በግልጽም ቀጥሏል። በተደረገው የደመወዝ ማስተካከያ 99.9% የሚሆነው መምህር አለመርካቱን በሥራ ማቆም አድማና በልዩ ልዩ መድረኮች ተቃውሞውንና ቅሬታውን በማሰማት አረጋግጧል። ይህ ቅሬታ አሁንም አልተዳፈነም ይበልጡንም ውስጥ ውስጡን እንደ ቋያ እሳት እየተፋፋመ ሄደ እንጂ።

ይህ በእንድህ እያለ ወያኔ/ ኢህአዴግ መምህሩን ሊወክል የማይችል የመምህራን ማህበር ተብዬ ተለጣፊ በአምሳሉ ጠፍጥፎ ከት/ቤት መሰረታዊ መምህራን ማህበር አንስቶ እስከ አገር አቀፍ ድረስ የራሱ አባል የሆኑ መምህራን ሙሉ ለሙሉ አመራሩን እንዲይዙና ማህበሩን እንዲቆጣጠሩ ቢያደርግም ማህበሩን ከካድሬ መምህራን አመራር ነፃ ለማውጣትና የገቢ ምንጩን ለማድረቅ መምህራን በራሳቸው ተነሳሽነት ከአባልነት አሰናብቱን የሚል ጥያቄ በአዲስ አበባና በአማራ ክልል በሚገኙ ትምሕርት ቤቶች የተጀመረው እንቅስቃሴ በራሳችን ገንዘብ መልሶ ራሳችንን አሳልፎ ለወያኔ/ኢህአዴግ ከሰጠን ማህበር ጋር በአባልነት መቀጠል አንፈልግም፤ የተቋቋመበትን የትምሕርት ጥራት የማስጠበቅ ፣ የአባላትን መብትና ጥቅማጥቅም የማስከበር ዓላማውን ዘንግቶ ከወያኔ ጉያ የተሸጎጠ ማህበር እኛን አይወክለንም የሚል መፈክር አንግበው በአገኙት አጋጣሚ ሁሉ እያካሄዱ ያለው ትግል ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል እንላለን።

ሌላው በትምሕርት ዘርፍ የሚታየው ግዙፍ ችግር የትምህርት ጥራት በኪሳራ ላይ መውደቅ ነው። ለትምህርት ጥራት መውደቅ ዋነኛው መንስሔ የትምህርት ፖሊሲው ችግር ሲሆን በተለይም ሕፃናት በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የመማር መብት የዓለም አቀፍ ድንጋጌ ስለሆነና ይህን ተከትሎ ወያኔ /ኢህአዴግ እተገብረዋለሁ በማለት ባወጣው ፖሊሲው ያካተተው በአፍ መፍቻ ቋንቋ የመማር መብት በሁሉም ክልሎች ለሁሉም የአገሪቱ ሕፃነት በእኩልነት ተግባራዊ አለመደረጉ ነው። ለምሳሌ ቀድሞ የወሎ ክፍለ ሀገር አካል የነበሩ በወያኔ አገዛዝ በጉልበት ወደ ትግራይ ክልል የተጠቃለሉ ቀበሌ ነዋሪዎች የሆኑ አማርኛ ተነጋሪዎች ወላጆች ልጆቻቸው የአፍ መፍቻ በሆነው ቋንቋቸው በአማርኛ እንዲማሩላቸው በተደጋጋሚ ቢጠይቁም ምላሽ ባለመግኘታቸው ልጆቻቸው በግዳጅ በትግርኛ ቋንቋ እንዲማሩ በመደረጉ ትምህርት ሊገባቸው አልቻለም።በመሆኑም በርካታ ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች በየዓመቱ ትምህርታቸውን ያቋርጣሉ። ይህ በአፍ መፍቻ ቋንቋ የመማር ዕድል መነፈግ በሁሉም የአገሪቱ ክልሎች የተከሰተ ስለሆነ ዓለም አቀፍ ድንጋጌንም ሆነ ወያኔ ተግባራዊ አደርጋለው የሚለውን የራሱን ሕገ መንግስት የጣሰ በመሆኑ በታሪክ ጥቁር ነጥብ ያስመዘገበና በሕግም የሚያስጠይቅ አገር የማጥፋትና ትውልድ የመግደል እኩይ ተግባር አንዱ መገለጫ ነው።

በሁሉም ክልሎች ሊባል በሚችል ሁኔታ ከ 1ኛ እስከ 4ኛ ክፍል የሚማሩ ተማሪዎች መድገም ስለማይፈቀድላቸው መምህሩ ወደ ሚቀጥለው ክፍል እንዲያሳልፋቸው ግዴታ ተጥሏል። ይህ አልበቃ ብሎ በአማራ ክልል በዚሕ በ2005 የትምህርት ዘመን የ 1ኛ ደረጃ መምራንን መስከረም ላይ የተረከብናቸውን ተማሪዎች እስከ ትምህርት ዘመኑ መጨረሻ አንድም ተማሪ ሳይጎድል ይዘን እንዘልቃለን ስትሉ ውል ተፈራረሙ መባላቸውና በገጠር የሚገኙ መምህራን ያለ ፍላጎታቸው በተፅዕኖ በግድ እንዲፈርሙ ሲደረግ በከተማ የሚያስተምሩ መምህራን ግን ጠንካረ ተቃውም በማሰማታቸው ውሉን ለመፈራረም ይህ መግለጫ እስከወጣበት ድረስ ፈቃደኛ አልሆኑም።ተማሪዎች ትምህርት የሚያቋርጡበት ምክንያት ብዙ ናቸው። ያንን መምራንን መቆጣጠር አይችሉም።የትም አገር ታይቶ የማይታወቅ ግዳጅ ነው። ተማሪውን ከትምህርት ገበታው እንዲገኝ የትምህርት ግብዓቶችን ማሟላት የተማሪዎችንና የመምህራንን የአካዳማዊ ነፃነትን ማክበር ነው መፍትሔው። የወያኔ ውል ፈርሙ ዓላማው መምህሩን ለማጥቃት ነው።ይህን መቃወም ያስፈልጋል።መምህራን እየወሰዱ ያሉትን እርምጃዎች በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ ይደግፋል።ሌላውም የሕብረተሰብ ክፍል ከጎናቸው መቆም ይጠበቅበታል።

ከዚህ በተጨማሪ መምህራን ከልዩ ልዩ የማሰልጠኛ ተቋማት በጥራትና በብቃት ሰልጥነው እንዲወጡ አለመደረጉ፣ የሥርዓተ ትምህርቱ ዝግጅት የተማሪዉን የትምህርት አቀባበል ችሎታ ዕድሜና አካባቢያዊ ሁኔታ ያላገናዘበ፣ ማስተማሪያ መጽሐፍቱ በይድረስ ይድረስ የተዘጋጁ፣በይዘት ግድፈት የታጨቁ ፣ የይዘት መዘበራረቅና የጽንሰ ሃሳብ ችግር የሚታይበት ፣ በበቂ የትምህርት መርጃ መሳሪዎች ያልተደገፈ፣ የመማሪያ ክፍሎች ሳቢና ማራኪ አለመሆን፣ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ አናሳ መሆን የትምህርቱን ጥራትና በእኩልነት መዳረስን በእጅጉ ጎድቶታል። ከልዩ ልዩ ተቋማት የሚመረቁ ተማሪዎች ሥራ ማጣትና ድንጋይ ማንጠፍ ( ኮብልስቶን ) ዶሮ እርባታ፣ ከብት ማድለብ፣... እንዲሰማሩ መደረጉ በዝቅተኛም ሆነ በከፍተኛ ደረጃ በመማር ላይ የሚገኙ ተማሪዎች የመማር ፍላጎት ከጊዜ ወደ ጊዜ እንዲያሽቆለቁልና ለትምህርትና ለትምህርት ባለሙያዎች ያላቸው አመለካከት እንዲቀንስ አተዋጽኦ በማድረግ ላይ ይገኛል። ለዚህ ማስረጃው ደግሞ በ2004 ዓ.ም የ10ኛ ክፍል ማጠናቀቂያ ፈተና ወስደው ወደ መሰናዶ ትምህርት ሊያስገባ የሚያስችል ውጤት ያላመጡት ተማሪዎች በቴክኒክና

ሙያ ት/ቤቶች ገብተው ለመማር አለመፈለጋቸው ነው። በዚህ ፍላጎት ማጣት በአማራ ክልል በሚገኙ ከ63 ባላነሱ የቴክኒክና ሙያ ት/ቤቶች በ2005 ዓ.ም ለመማር የተመዘገቡት ተማሪዎች ቁጥር ካለፉት ዓመታት ጋር ሲነጻጸር ከ70-80% ቀንሶ መገኘቱ ነው። ይህም የትምህርትና ስልጣና ሥርዓቱ ምን ያህል አደጋ ላይ እየወደቀ እንደሆነ አመላካች ነው።

በሥልጣን የሚገኙ የወያኔ መሪዎች ልጆቻቸውን በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር በተሻሉ ትምህርት ቤቶች እያስተማሩ የድሃው የሕብረተሰብ ልጅ ግን ጥራት ያለው ትምህርትም የሥራ ዕድልም በማጣቱ ተስፋ ቆርጦ የተቀመጠበት፣ የእውቀት ድሃ እንዲሆን የተፈረደበት ፣ የትምህርት ፍላጎቱና ተነሳሽነቱ ተሟጦ ያለቀበት ፣ የአገሪቱ መጻኢ ዕድል አሳሳቢ ደረጃ ላይ የደረሰበት ፣ በትምህርት የታነጸ ተተኪ ትውልድ ለማግኘት የምንቸገርበት የታሪክ ወቅት ላይ ነው የምንገኘው። የትምህርት ሥራ ውጤቱ እንደ ሌላ መስሪያ ቤት በአጭር ጊዜ የሚታይ ካለመሆኑ ጋር ዛሬ ወያኔ በትምህርቱ ዘርፍ የፈጸመው አገር የማጥፋትና ትውልድ የመግደል እርምጃ ኮብልስቶን አንጣፊና የእውቀት አድማሳቸው ውስን የሆኑ ዜጎችን በማፍራት እየታየ ነው።

በኢህአዴግ የአገዛዝ ዘመን በትምህርትና በማስተማር ሙያ ላይ የተፈጸመውንና እየተፈጸመ ያለውን ታሪክ ይቅር የማይለውን በደልና አድልዎ በዚች አጭር ጽሑፍ ለመዘርዘር መሞከር አባይን በጭልፋ ይሆናል።ስለሆነም ይህን አገርን የማጥፋትና ትውልድን የመግደል ሴራ ማክሸፍ የሁሉም ዜጋ ብሔራዊ ግዴታ ነው። መምህራን ፣ ተማሪዎች፣ ወላጆች ፣ የትምህርቱ ሥራ የሚመለከታቸው አካላት በቅንጅት መታገልና አገርንና ወገንን ከውድቀትና ከጥፋት መታደግ እንዲችሉ በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ ጥሪውን ያቀርባል።

እንንቃ- በስልት እንደራጅ !!
በጋራ ጠላት ላይ በጋራ እንነሳ!!
መምህራንና ኢመማ በመራራ ትግል ነፃ ይወጣሉ!!!

ለአስተያየትና ጥያቄዎቻችሁ በ eta1941@yahoo.com ኢሜል አድራሻ ይጻፉ